# ትንቢተ ናሆም (55)

## ጥናት አንድ ናሆም 1፡1-15

የጥናት ዓላማ፡- አንዳንድ ጊዜ አማኝ መከራና ጭንቀቱ ከሚችለው በላይ እንደሆነ፤ ወይም ደግሞ መከራ በተደጋጋሚ በሚያገኘው ጊዜ ሰይጣን በአዕምሮው ውስጥ የሚዘራው ዘር የእግዚአብሄርን መልካምነት ከጥያቄ ውስጥ ማስገባት በመሆኑ፤ አማኝ ሁልጊዜ የዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ሲገባ ማስታወስ የሚኖርበት ነገር ቢኖር፤ እግዚአብሄር ለሚታመኑትና እርሱን ተስፋ ለሚያደርጉት መልካም እንደሆነ ማሰብ መሆኑን ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “እርሱን ተስፋ ለሚያደርጉት፤ ለሚፈልገውም ሰው እግዚአብሄር መልካም ነው።” ሰቆ ኤር 3፡25

1. ትንቢተ ናሆም 1፡1-15 በአንድነት ይነበብ። በቁ1 ላይ በምናነብበት ጊዜ እግዚአብሄር ለነብዩ ናሆም እንዲያስተላልፍ የሰጠው መልዕክት እንደ አብዛኞዎቹ ነቢያት በእግዚአብሄር ሕዝብ ላይ ያተኮረ እንዳልሆነ እናያለን፤ ታዲያ የናሆም የትንቢቱ ትኩረት በማን ላይ ነው? ይህችን ናሆም ትንቢቱን ያመጣላትን ከተማ እንዲሁ እግዚአብሄር በሌላ ጊዜ ደግሞ የተናገራትን ጊዜ የምታስታውስ ከሆነ ሁኔታውንንና በማን በኩል መልዕክቱን እንዳስተላለፈላት ተናገር።
2. በማንኛውም ህብረተሰብ መካከል ቅናት የሚለው ሃሳብ ክፉ እንጂ መልካም የሆነ ትርጓሜ እንደማይኖረው የታወቀ ሲሆን፤ መጽሐፍ ቅዱሳችንም ቢሆን በ1ኛ ቆሮ 3፡3፣ ሮሜ 1፡29ንና የመሳሰሉት ክፍሎች በምንመለከትበት ጊዜ “ቅናት” የሚባለው ሃሳብ መልካም እንዳልሆነ እንረዳለን፤ ታዲያ እግዚአብሄር መልካም አምላክ ነው ብለን የምናምን ከሆነ፤ በናሆ 1፡2 ላይ “እግዚአብሄር ቀናተኛና ተበቃይ አምላክ ነው” በዘፀ 34፡14 ላይም “ስሙ ቀናተኛ የሆነው…” በማለት ስለ እግዚአብሄር ማንነትና ባህርይ መናገሩ ምን ለማለት ፈልጎ እንደሆነ ነው የምትረዳው?
3. ነብዩ ናሆም በቁ2-6 ላይ ያሰፈረውን ስለ እግዚአብሄርን ማንነት፣ ችሎታ፣ ትልቅነትና የመሳሰሉትን ነገሮች ሁሉ በምናነብበት ጊዜ ከሁለት አንጻር መመልከት እንችላለን፤ እንደ እግዚአብሄር ልጅና እንደ አማኝ ሆነህ ስታነበው ይህ ክፍል መጽናናት ሊሆንህ የሚችለው በምን መንገድ ነው? ይህንኑ ክፍል ደግሞ በእግዚአብሄር ላይ በዓመጽ ለሚኖር፣ በትዕቢት፣ በኩራትና፣ በማን አለብኝነት ህይወቱን ለሚመራ ሰው ከአማኝ በተቃራኒ፤ የፍርሃት ምንጭ የሚሆንበት በምን መንገድ እንደሆነ ተናገር።
4. ሰቆ ኤር 3፡25 ትን ስናነብ ነብዩ ናሆም በቁ7-8 ላይ ከሚናገረው ሃሳብ ጋራ እንደሚስማማ እንመለከታለን፤ ይህ ክፍል የእግዚአብሄርን መልካምነት ከመናገር በተጨማሪ፤ መልካምነቱና በጭንቅ ጊዜ መሸሸጊያ የሚሆንላቸው ለምን ዓይነት ሰዎች እንደሆነ ነው የሚነግረን? በእነዚህ ቁጥሮች ማለትም በቁ7-8 ላይ ስናነብ መልዕክቱ የመጣላትን የነነዌን ከተማ ነብዩ ከየትኛው ወገን እንደሆነች አድርጎ ነው የሚናገረው? በህይወትህ እግዚአብሄር በጨነቀህ ጊዜ መሸሸጊያ ሆኖልህ አይተኸው ታውቃለህ ወይ?
5. በአጠቃላይ የነነዌ ከተማን ብቻ በመመልከት ከዮናስ ጊዜ አንስቶ ናሆም የተናገረው የፍርድ ቃል እስከተፈጸመበት ጊዜ ድረስ ያለውን እግዚአብሄር ከዚህች ከተማ ጋራ ያሳለፈውን ሁኔታ ስንመለከት፤ ማስተዋል የምንችላቸውና በዚህ ሁሉ ሁኔታ ውስጥ ተገልጠው የሚታዩህ የእግዚአብሄር ባህርያት ምን ምን እንደሆኑ ተናገር።
6. ቁ11 ላይ “ነነዌ ሆይ፤ በእግዚአብሄር ላይ የሚያሴር ክፋትንም የሚመክር ከአንቺ ዘንድ ወጥቷል።” በማለት ሲናገር እናያለን። ይህንን አነጋገር ስታይ ነብዩ የሚናገረው እውነት ከነነዌ የሚወጣው ሰው እግዚአብሄርን ከዙፋኑ ለመጣል በእርሱ ላይ ክፋትን እየመከረ ነው ማለቱ ነው ወይስ ሌላ ሃሳብ ያዘለ ነው ትላለህ? አንዳንዶች እግዚአብሄርን በአፍቃሪነቱ ብቻ ያውቁታል፤ ታዲያ ትንቢተ ናሆም ለእንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ሊያስተምር የሚችለው ተጨማሪ እውነት ምንድነው ትላለህ?
7. ቁ13-15 ስናነብ የይሁዳ ቀንበር ከአንገቱ ላይ እንደሚሰበርና፤ ሰንሰለቱንም ደግሞ እግዚአብሄር ራሱ እንደሚበጥስለት ሲናገር፤ ለጠላቱ ለነነዌ ደግሞ የስም መጠሪያ እንኳን እንዳይኖረው እንደሚያደርግ ይነግረናል። ታዲያ እግዚአብሄር የህዝቡን ጠላት ከጣለለትና እርሱንም በከፍታ ሥፍራ ካስቀመጠው በኋላ ከህዝቡ ስለሚጠብቀው ነገር ከእነዚህ ቁጥሮች ምን ይነግሩናል?
8. መለስ ብለን ቁ7ትን ስንመለከት፤ አማኞች በጭንቀትና በመከራ ውስጥ ሲያልፉ ጠላት ሰይጣን እንዲጠራጠሩት የሚያደርገውን ከእግዚአብሄር መሰረታዊ ባህርያት ውስጥ ናሆም አንዱን በዚህ ቁጥር ላይ አስፍሮልናል፤ ነብዩ የሚናገርለት ባህርይ ምንድነው? ከምታልፍበት ጭንቀት የተነሳ ጠላትህ ሰይጣን የእግዚአብሄርን መልካምነት እንድትጠረጥረው ፈትኖህ ያውቃል ወይ? የአማኝ መከራና ጭንቀቱ ምንም እንኳን የከበደ ቢሆን፤ የእግዚአብሄርን መልካምነት ጥያቄ ላይ ሊያመጣ የሚችለው ጠላታችን ሰይጣን ብቻ ነው።

<u>ጥናት ሁለት ናሆም 2፡1-3፡19</u>

የጥናት ዓላማ፡- ነነዌ በአካባቢዋ የሚገኙትን መንግሥታት በሙሉ አስከፊ በሆነ ጭቆና በማዋረዷ ምክንያት እግዚአብሄር መልሶ በዚያው መንገድ እንደፈረደባት ሁሉ፤ በሌሎች ላይ ለምናሳየው መልካምም ሆነ ክፉ ነገር የዘራነውን ማጨዳችን የማይቀር እንደሆነ ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “የአሶር ንጉስ ሆይ እረኞችህ አንቀላፉ፤ መኳንንቶችህ አርፈው ተኙ፤ ሕዝብህ ሰብሳቢ አጥተው ተበትነዋል፤ ቁስልህን ሊፈውስ የሚችል የለም ስብራትህም ለሞት የሚያደርስ ነው ስለአንተ የሰማ ሁሉ በውድቀትህ ደስ ብሎት ያጨበጭባል፤ ወሰን የሌለው ጭካኔህ ያልነካው ማን አለና” ናሆ 3፡19

1. ትንቢተ ናሆም 2፡1-3፡19 በአንድነት ይነበብ። በቁ2፡1 ላይ እግዚአብሄር በነብዩ በኩል ነነዌ ልታደርግ የምትችለውን ሁሉ እንድታደርግ ሲነግራት፤ እውነት እግዚአብሄር ሊያመጣ ካለው ፍርድ እርሷ በምታደርገው የተለያዩ ነገሮች ሊመጣባት ካለው ነገር መዳን ትችላለች ለማለት ነው ወይ? ካልሆነስ ታዲያ ይህንን ንግግር ሲናገራት ምን ለማለት ፈልጎ ይመስልሃል? በቁ2 ላይ እግዚአብሄር የያዕቆብ ቤት ክብር እንደሚመለስ ሲናገር እንመለከታለን፤ በቁ1 ላይ የተነገረው በነነዌ ላይ ለማፌዝ እንጂ፤ ከእግዚአብሄር ዘንድ ሊመጣ ላለው ጥፋት ነነዌ ምንም ለማድረግ እንደማትችል ከሰጠነው መልስ ጋራ በምን ዓይነት ነው ቁ2 የሚስማማ መሆኑን የምናየው?
2. ከ3-7 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ ስንመለከት፤ በነነዌ ላይ ሊመጣ ያለውን ፍርድና ውድቀት የማይቀር ነገር እንደሆነ በእርግጠኛነት ከማሳየት አልፎ፤ እንዲያውም ገና ሁኔታው ከመከሰቱ አስቀድሞ እንደ ተከናወነ ነገር በማድረግ የሚያረጋግጥልን ክፍል የትኛው ነው? በቁ5 ላይ የታወቁትና ምርጥ እንደሆኑ የሚታወቅላቸው የአሶር ተዋጊዎች ከተማይቱን ከሚመጣው ወራሪ ጠላት እንዲከላከሉ ጥሪ እንደሚደረግላቸው እናነባለን፤ ታዲያ የእነዚህ ምርጥ ተዋጊዎች መምጣት ስለሚያስገኘው ውጤት ማየት የምንችለው ነገር ምንድነው? እግዚአብሄር ህዝቡን ሊረዳ ከተነሳ ማንኛቸውም የሲያል ሰራዊት ቢሰበሰብ ሊያቆመው እንደማይችል ልንረዳ ያስፈልገናል።
3. በቁ8-10 ላይ ስናነብ በተለይም ቁ10c ሲታይ በነነዌ ከተማ ላይ እየሆነ ስላለው ነገር ሰባት ነገሮችን ጸሐፊው የዘረዘረ ሲሆን፤ ሶስቱ ባላት ንብረት ላይ በማተኮር፤ አራቱ ደግሞ ልክ ከተማዋን እንደሰው በማስመሰል በማንነቷ ላይ የደረሰውን ያሳዩናል፤ እነዚህ የተነገሩት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ በሁለት በመክፈል አስረዳ። በቁ11 እና በቁ12 ላይ አሶራውያንን ለመመሰል ነብዩ ናሆም ሲጠቀምበት የምንመለከተው አንድ ነገር እናያለን፤ ይህ የአሶር ሕዝብ የተመሰሉበት ነገር ምንድነው?
4. ከታሪክ እንደምንረዳው የአሶርን ንጉስ በመገርሰስ እንዳልነበረ ያደረጉት በ612 ዓ.ዓ ባቢሎናውያን፣ ከለዳዊያንና የሜዶ ፐርሺያ መንግሥታት እንደሆኑ እናውቃለን፤ ሆኖም በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በተለይም ቁ13ትን በምንመለከትበት ጊዜ ነነዌን ያንበረከኳት እነዚያ ሁለት መንግሥታት እንዳልሆኑና ሌላ ሃይል እንደነበረ ያመለክተናል፤ ታዲያ እነዚህ መንግሥታት ካልሆኑ የአሶርን መንግሥት ያኮታኮተው ማን ነው? የአወዳደቃቸውን ዝርዝር ሁኔታ ሲናገር ይህ ቁጥር በከተማይቱ ላይ ምን ምን እንደሚሆን ነው የሚያውጀው?
5. በ3፡1 ላይ ይህችን ፍርድ ሊያመጣባት እየተዘጋጀ ያለችውን የነነዌ ከተማ እግዚአብሄር በባሪያው በናሆም በኩል ለማስተዋወቅ ሲጠቀምባቸው የምንመለከታቸው ሃሳቦች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር። በቁ2-3 ላይ ደግሞ ነብዩ በዚህች ከተማ ላይ እግዚአብሄር ሊመጣ ያለውን ነገሮች በሙሉ ልክ እንደተከናወነ ነገር፤ “የሞተው ብዙ ነው፣ ሬሳ በሬሳ ሆኗል…) አድርጎ ነው ሲናገር የሚታየው፤ ገና ያልሆነውንና ወደፊት ሊሆን ያለውን ነገር እንዴት ነው ናሆም እንደሆነ አድርጎ የሚናገረው? አንተስ እግዚአብሄር በቃሉ ውስጥ የተናገረውን እውነት ምን ያህል በእምነት ተቀብለህ ልክ እንደሆነ ነገር አድርገህ ተስፋውን ትይዛለህ?
6. በቁ4-7 ውስጥ በዚህች ከተማ ላይ እግዚአብሄር ሊያደርግ ያለውን ነገር ጠለቅ ባለ ዝርዝር ሲናገር እናየዋለን። እግዚአብሄር በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የሚናገራቸውን ሃሳቦች ሁሉ በአንድ ቃል ብቻ ለመግለጽ ሞክር ብትባል ምን ትላለህ? ነነዌ፣ አይ ይህ ነገር በእኔ ላይ ሊመጣ አይችልም በሚለው ሃሳብ ራሷን እንዳታታልል ሊያደርጋት እግዚአብሄር በቁ8-10 የተጠቀመበት ምን መንገድ ታያለህ?
7. ቁ13 “እነሆ ጭፍሮችሽ ሁሉም ሴቶች ናቸው” ሲል በአሶር ጭፍራ ውስጥ ወንድ የሚባል የለም፤ ጭፍሮቹ ወይም ወታደሮቹ ሁሉ ሴቶች ናቸው ማለቱ ነው ወይ? ካልሆነስ እግዚአብሄር ምን ለማለት ፈልጎ ይመስልሃል?
8. በቁ3፡19 ላይ እግዚአብሄር በነነዌ ላይ የሚያደርገውን በመስማት አካባቢው ሁሉ ደስተኛ እንደሚሆንና እንደሚያጨበጭብ ናሆም ይናገራል። በነነዌ ውድቀትና በማያዳግም መንገድ ቅጣት መቀበሏ ለምን ይመስልሃል የአካባቢው መንግሥታት ሁሉ ደስተኛ የሆኑት? አንተስ በህይወትህ በሰፈርክበት መስፈሪያ የተሰፈረለህን ጊዜ ታስታውሳለህ ወይ? ማቴ 7፡1-2 “…በምትፈርዱበት ፍርድ ይፈረድባችኋል፤ በምትሰፍሩበትም መስፈሪያ ይሰፈርባችኋል።” እንደሚለው፤ እግዚአብሄር አምላክ በሌሎች አቅም በሌላቸው ላይ የምናሳየውን ጉልበትና ጭቆና፤ በዚያው መጠን በእኛ ላይ ሊመልስብን እንደሚችል መዘንጋት የለብንም።